በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡-209647

ቀን፡-28/03/2014ዓ.ም

**ዳኞች፡-** እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ አምሳሉ ቶሮ-አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የብርብር ከተማ አንድነት ንግድ ማሕበር - ተወካይ አሜጫ አይጎት ቀረቡ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሠኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 33612 ሚያዝያ 21 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 35627 ሠኔ 10 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የከተማን ይዞታ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በምዕራብ ዐባያ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፤ የአሁን አመልካች ደግሞ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ያቀረበው ክስ ይዘት በአጭሩ፡- አዋሳኙ በክሱ የተገለጸ እና በምዕራብ ዓባያ ወረዳ ብርብር ከተማ ቀጠና 1

ውስጥ የሚገኝ አጠቃላይ ስፋቱ 1234 ካ.ሜ የሆነ የድርጅት ይዞታ ያለው መሆኑን፤ አመልካቹ በጥቅምት ወር 2011 ዓ.ም 9.6 x 1.1 = 10.56 ካ.ሜ ድንበር አልፎ የያዘበት መሆኑን፤ አመልካች አላግባብ የያዘውን ይዞታ እንዲለቅ በተደጋጋሚ ተጠይቆ ፈቃደኛ አለመሆኑን በመግለጽ አልፎ የያዘውን ይዞታ እንዲለቅ እና ወጪ ኪሳራ የማቅረብ መብቱ እንዲጠበቅ ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በሰጡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው ውድቅ የተደረገ ሲሆን በፍሬነገሩ ላይ በሰጡት መልስ ደግሞ አመልካች ይዞታውን የተመራሁት በ1989 ዓ.ም ነው፤ በ1992 ዓ.ም በድንበር ክርክር ተነስቶ በቀበሌ አስተዳደር ኮሚቴ ታይቶ አመልካች 1200 ካ.ሜ የቀድሞ ምሪት እንዳለኝ ካርኒ አቅርቤ ተጠሪ ደግሞ የቀድሞ ምሪቱ 250 ካ.ሜ መሆኑ ታይቶ በትርፍነት የያዘው 522 ካ.ሜ እንዲመልስ ተወስኖበታል፤ አመልካች በወቅቱ በስተሰሜን በኩል ድንበር ያላለፍኩ መሆኑም በማሕበራዊ ፍርድ ቤት ተወስኖልኛል፤ ተጠሪ ያቀረበው ማስረጃ በማጭበርበር የተገኘ ነው፤ ስለሆነም ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የግራቀኙን ምስክሮች ከሰማ እና የሚመለከተው የአስተዳደር አካል ቦታው ድረስ በመሄድ አጣርቶ ምላሽ እንዲልክለት ካደረገ በኋላ ከተጠሪ ምስክሮች ቃል እና  የሚመለከተው አካል ከሰጠው ምላሽ አመልካች የተጠሪን ድንበር ማለፉን መገንዘብ ተችሏል፤ አመልካች ባቀረባቸው ምስክሮችም ሆነ በሰነድ ማስረጃ ድንበር አለማለፉን አላስረዳም፤ የማሕበራዊው ፍርድ ቤት ውሳኔ የራስጌ ማሕተም የሌለበት እና ዳኞቹ እነማን እንደሆኑ የማይገልጽ ሲሆን በ1992 ዓ.ም ማሕበራዊ ፍርድ ቤቱ ያልተቋቋም በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፤ አመልካች ከይዞታው ውጪ አልፎ የያዘው 9 ሜ x 0.5 ሜ= 4.5 ካ.ሜ ሲሆን ወደ ተጠሪ ይዞታ አልፎ የያዘውን 0.5 ሜትር የሆነ ይዞታ ለተጠሪ ሊለቅ ይገባል፤ አመልካች በተደጋጋሚ ይዞታውን እንዲለቅ ተጠይቆ ፈቃደኛ አለመሆኑን ተጠሪ በማስረጃ ያላረጋገጠ በመሆኑ ይህን አስመልክቶ ያቀረበው የወጪ ኪሣራ ጥያቄ ተቀባይን የለውም ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለጋሞ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤተቱታ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪም የስር ፍርድ ቤቱ ወጪ ኪሳራን አስመልክቶ የሰጠውን ውሰኔ በተመለከተ መስቀለኛ ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ተጠሪ ወጪ ኪሳራን በሚመለከት ያቀረበውን መስቀለኛ ይግባኝ ውድቅ አድርጎ ዋናውን ጉዳይ በሚመለከተ ደግሞ የጋሞ ዞን ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ ስለጉዳዩ አጣርቶ ሙያዊ አስተያየት እንዲልክለት ካደረገ በኋላ አመልካች በይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃው ላይ 220.05 ካ.ሜ ይዞታ እንዳላቸወ የተገለጸ ሲሆን በመሬት ላይ ደግሞ 227.05 ካ.ሜ ሆኖ በብልጫነት 6.55 ካ.ሜ ይዘዋል፤ የተጠሪ ይዞታ 1240 ካ.ሜ መሆን ሲገባው 4 ካ.ሜ በስህተት ተደምሮ 1243 ካ.ሜ ሆኗል፤ የቀረበው ሪፖርት ተጠሪ ካለው ይዞታ የተቀነሰበት ይዞታ እንደሌለ የሚያስረዳ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቱ አመልካች አልፎ የያዘውን የተጠሪ ይዞታ እንዲለቅ ሲል የሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት ሽሮታል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ከተለያዩ አካላት የተውጣጡ ባለሙያዎች ስለጉዳዩ አጣርተው

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እንዲያቀርቡለት እና አስቀድሞ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት መግለጫ የሰጡ ሁለት ባለሙያዎች ማብራሪያ እንዲሰጡት ካደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተጣራው ውጤት አመልካች አልፎ ይዞታል የተባለውን የይዞታ መጠን በሚመለከት የተለያየ ቢሆንም አመልካች የተጠሪን ይዞታ አልፎ መያዙ ተረጋግጧል፤ ስለሆነም የስር ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ገፍቶ የያዘው የተጠሪ ይዞታ የለም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት ሽሮ አመልካች በምዕራብ ዓባያ ወረዳ ብርብር ከተማ ቀጠና 01 ውስጥ ከተጠሪ ድርጅት አልፎ የያዘውን 1.1 ሜ x 9.55 ሜ =10.505 ካ.ሜ ይዞታ እንዲለቅ ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በተራቸው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ውሳኔው ሳይለወጥ ቀርቷል፡፡

አመልካች ሠኔ 21 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጠየቀው ዳኝነት በወረዳው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ ይጽናልኝ የሚል ነው፤ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች 10.505 ካ.ሜ ይዞታ ለተጠሪ እንድለቅ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የስር ወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች 0.5 ሜትር አልፎ የያዘውን የተጠሪ ይዞታ እንዲለቅ በማለት የሰጠውን ውሳኔ ለማስለወጠ አመልካች ይግባኝ ብለው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻረበት ሁኔታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች 10.505 ካ.ሜ የሆነ ይዞታ ለተጠሪ እንዲለቅ የመወሰኑን አግባብነት ከመሠረታዊ የክርክር አመራር ሥነ ሥርዓት ጋር በማገናዘብ ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

ተጠሪ መስከረም 25 ቀን 2014 ዓ.ም የሰጠው መልስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካች 10.56 ካ.ሜ ከተጠሪ ይዞታ ላይ አልፎ የያዘውን ይዞታ እንዲለቅ ክስ ቀርቦበት የወረዳው ፍርድ ቤት 0.5 ሜትር አልፎ የያዘውን ይልቀቅ ብሎ ወስኗል፤ አመልካች ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ የወረዳው ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር መስቀለኛ ይግባኙን ሲሰርዝ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቤአለሁ፤ ይግባኙ የቀረበለት  ፍርድ ቤትም ተጨማሪ ማጣራት አድርጎ በስር ወረዳው ፍርድ ቤት በጠየቅኩት ዳኝነት መሠረት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ስለሆነ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ እንደተቻለው አመልካች የተጠሪን ይዞታ አልፎ የያዘበት ስለመሆኑ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው የወረዳው ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተረጋግጧል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10/1 መሠረት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ስልጣን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም እንጂ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የሌለው በመሆኑ አመልካች የተጠሪን ይዞታ አልፈው ይዘዋል? ወይስ አልያዙም? የሚለው በዚህ ችሎት የሚጣራ አይደለም፡፡

በሌላ በኩል በሰበር አጣሪው ችሎት ከተያዘው ማስቀረቢያ ነጥብ አንጻር የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ሊለቁት የሚገባውን የይዞታ መጠን 0.5 ሜትር ነው በማለት በሰጠው ውሳኔ ላይ ተጠሪ ስርዓቱን ጠብቆ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝ በሌለበት ሁኔታ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በከፍተኛው ፍርድ ቤት መሻሩን ተከትሎ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረበው ይግባኝ መነሻነት አመልካች ከተጠሪ ድርጅት አልፎ የያዘውን 1.1 ሜ x 9.55 ሜ =10.505 ካ.ሜ ይዞታ እንዲለቅ በማለት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የይግባኝ ክርክሮች የሚመሩበትን ሥርዓት ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. በደቡብ ብሔሮች ብሔረሠቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 33612 ሚያዝያ 21 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 35627 ሠኔ 10 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካቾ ለተጠሪ ሊለቁት የሚገባው የይዞታ መጠን በወረዳው ፍርድ ቤት ላይ የተገለጸውን የይዞታ መጠን ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. ሐምሌ 14 ቀን 2013 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ
   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ
   - ሄ/መ                    የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም